# የተወሰነ ስፍራ ግቤት

Standard

**ይዘቶች**


**1 መመርያ ........ 3**

**2 ፍችዎች ........ 3**

**3 ሃላፊነቶች ........ 4**

3.1 ተቆጣጣሪ/ለስራ ሃላፊነት የሚወስደው ሰው (PICW) ........ 5

3.2 ተቀጣሪ/ ሥራ ተቋራጭ ........ 5

3.3 ቆሞ ተመልካች ሰው ........ 6

**4 አሰራር ........ 6**

4.1 የተወሰነ ቦታ ከማግባት በፊት ........ 6

4.2 በተወሰነ ስፍራ መግቢያ ስራ ወቅት ........ 7

**5 የጤና አቋም እና ምላሽ ........ 7**

**6 ተጋላጭነት ግምገማ እና እቅድ ........ 7**

**7 የመግቢያ ፍቃድ ........ 7**

7.1 የመግቢያ ፍቃድ አስገዳጅ ይዘቶች ........ 8

**8 የግል መከላከያ መሳርያ ........ 8**

8.1 የPPE ልየታ እና ምርጫ ........ 9

**9 መሳሪያዎች እና መገልገያዎች ........ 9**

**10 ስልጠና ........ 10**

**11 ክትትል እና ግምገማ ........ 10**

**12 መዝገቦች ........ 10**

**13 የለውጥ መረጃ ........ 10**



© Ericsson AB 2021

ሁሉም መብቶች የተጠበቁ ናቸው። በዚህ ሰነድ ውስጥ ያለው መረጃ የኤሪክሰን ንብረት ነው እና ያለ ማስታወቂያ ሊለወጥ ይችላል። ኤሪክሰን ለእውነት ስህተቶች ወይም የጽሁፍ ስህተቶች ምንም አይነት ሃላፊነት አይወስድም።

# 1 መመርያ

ይህ መመሪያ በግንባታ እና በሲቪል ሥራ ወቅት ወይም የጥገና ሥራዎች ጊዜ ወደ ውስን ቦታዎች ከመግባት ጋር የተያያዙ አደጋዎች  ኤሪክሰንን በመወከል  ተከታታይነት ባለው እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ እየተከናወኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አነስተኛውን መስፈርቶች ያብራራል ።

በውስብስብ እና የተለያዩ ህጋዊ ገጽታዎች ፣በአከባቢ የግንባታ ደንቦች ፣ በሲቪል ደንቦች እና ለግንባታ እና ለጥገና ተግባራት በሚውሉ መስፈርቶች ምክንያት ይህ መስፈርት የሙያ ጤና እና ደህንነት (OHS) ገጽታዎች ብቻ እቀዳ ፣ አተገባበር እና አያያዝ ላይ ያተኩራል ።

ለግለሰብ ፕሮጀክቶች መጠን እና ውስብስብነት ትኩረት የሚሰጥ ይሆናል።

ያለ ቆሞ ተምልካች ሰው ውስንነት ያላቸው ቦታዎች ውስጥ የመግባት እንቅስቃሴዎች መቼም ሊሰሩ አይገባም።

# 2 ፍችዎች

ውስን ቦታ - ውስን ቦታ የተዘጋ ወይም በከፊል የተዘጋ ቦት ሆኖ፡

- በመጀመሪያ ለስራ ቦታ ተብሎ ያልታቀደ ወይም ያልታሰበ  ነው፣
- የተወሰነ ወይም የተከለከለ የመግቢያ ወይም መውጫ መንገድ ያለው እና ለተከታታይ መኖሪያ ያልታቀደ ነው፣
- ጎጂ ሊሆኑ የሚችሉ በካዮች ያለው፣ ደህንነቱ ያልተጠበቀ የኦክሲጅን መጠን ያለው ከባቢ አየር ወይም መዋጥን ሊያስከትሉ የሚችሉ የተከማቹ ንጥረ ነገሮች ሊኖረው ይሚችል፣
- ጎጂ ከባቢ አየር ያለው ወይም ሊኖረው የሚችል፣
- ገቢን ሊውጥ የሚችል ቁስ ያለው፣
- ወደ ውስጥ በሚያዘነብሉ ግድግዳዎች ወይም ወደ ታች የሚያጋድል እና ወደ አነስተኛ መስቀለኛ ክፍል የሚገናባ መሬት ያለው ገቢ ወጥመድ ውስጥ እንዲገባ ወይም እንዲታፈን የሚያስችል ውስጣዊ ውቅር አለው፡ ወይም፣
- እንደ ክትትል የማይደረግለት ማሽን፣ የተጋለጠ የኤሌክትሪክ መስመር፣ ወይም የሙቀት ጭንቀት አይነት ሌላ የተለዩ ከባድ የድህንነት ስጋቶች አለው።

የሚከተለው የተወሰኑ ቦታዎች የሚባሉትን አንድ አንድ ቦታዎች ዝርዝር ነው፡

- የመዳረሻ ቀዳዳዎች፣
- ቧንቧዎች፣
- የመሬት ውስጥ መጋዘኖች፣
- ዋሻዎች፣
- የፍሳሽ ማስወገጃ፣

- ቀዝቃዛ ማከማቻ ክፍል፣ እና
- በዮች ።

አደጋ - አደጋ በየሆነ ሰው ወይም የሆነ ነገር ላይ ማንኛውም አይነት ሊደርስ ለሚችል ብልሽት፣ ጉዳት ወይም አሉታዊ የጤና ውጤቶች ምንጭ ነው።

ተጋላጭነት - አንድ ሰው ለአደጋ ሲጋለጥ ሊጎዳ ወይም አሉታዊ የጤና ውጤት ሊያጋጥመው የሚችልበት አጋጣሚ ወይም እድል ነው። ይህም ከንብረት ወይም መሳሪያ መጥፋት ወይም በአከባቢው ላይ ጎጂ ውጤቶችን ለሚያስከትሉ ሁኔታዎችም ሊመለከት ይችላል።

በካይ - ብክለት በአጋጣሚ ወይም ሆን ተብሎ ወደ አየር ፣ ውሃ ፣ አፈር ወይም ምግብ ሲገባ ለሰው ወይም ለህያው ፍጥረታት ጎጂ የሚሆን ባዮሎጂያዊ ፣ ኬሚካላዊ ፣ አካላዊ ወይም ራዲዮሎጂያዊ ንጥረ ነገር ነው።

የመቀጣጠል ክልል - በላይኛው (UEL) እና በታችኛው (LEL) የተቀጣጣይ ገደቦች መካከል ተቀጣጣይ የእንፋሎት ወይም የጋዝ-አየር ድብልቅ ክልል ‹ተቀጣጣይ ክልል› በመባል ይታወቃል ፣ ብዙውን ጊዜ ‹ፈንጂ ክልል› ተብሎም ይጠራል።

የሙቀት ስራ - ብየዳ፣ ሙቀት ወይም ኦክሲጅንን ተጠቅሞ መቁረጥ፣ ማጋል እና ሌሎች የእሳት ወይም የፍንዳታ አደጋ ተጋላጭነት ሊጨምሩ የሚችሉ እሳት የሚፈጥሩ ወይም የእሳት ፍንጣሪ የሚፈጥሩ ስራዎች።

ደህንነቱ የተጠበቀ የኦክሲጅን ደረጃ - በተለመደው የከባቢ አየር ግፊት በ 19.5 በመቶ አየር ውስጥ ያለው አነስተኛ የኦክስጂን ይዘት (ከ 19.8 ኪፓ (148 ሚሜ ኤችጂ) ከፊል የኦክስጂን ግፊት (ፒኦ 2) ጋር እኩል ሲሆን እና በተለመደው የከባቢ አየር ውስጥ በ 23.5 በመቶ አየር ውስጥ ከፍተኛው የኦክስጂን ይዘት ግፊት (ከ 23.9 ኪፓ (179 ሚሜ ኤችጂ) ከፊል የኦክስጂን ግፊት (ፒኦ 2) ጋር እኩል ሲሆን።

ከተለመደው የከባቢ አየር ግፊት በጣም ከፍ ባለ ወይም ዝቅ ባለ ግፊት የባለሙያ መመሪያ ሊፈለግ ይገባል።

ልብ ይበሉ፡ የአየር ጥራቱ የተበከለ ይሆናል ብሎ የተጠረጠረ የትኛውም ውስን ቦታ ውስጥ መግባት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ማንም ሰው ወደ ተወሰነው ቦታ ሳይገባ በፊት የአየሩ ጥራት ሊፈተን እና በስራው ጊዜ በተከታታትይ ሊገመገም ይገባል።

ቆሞ ተመልካች ሰው - ተግባራዊ ሊሆን ከቻለ ከውስጥ ካሉት ጋር ያለማቋረጥ መገናኘት የሚችል እና የሚከታተል ከተወሰነው ቦት ውጭ እና አቅራቢያ እንዲቆይ የተሰየመ፣ ብቁ ሰው። በተጨማሪም አስፈላጊው የነፍስ አድን አሰራሮችን ያስጀምራል እና በተወሰነ ቦታ በሚሰራበት እና በሚገባበት ወቅት ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን ያንቀሳቅሳል እና ይቆጣጠራል።

# 3 ሃላፊነቶች

አስተዳሪዎች ለሚከተሉት ሃላፊነት ይወስዳሉ፡

- በእነርሱ ስር ያሉት ሁሉም ውስን ቦታዎች መለየታቸውን ማረጋገጥ።፣
- ለተለዩ ውስን ቦታዎች የአደጋ እና ተጋላጭነት ግምገማ ማካሄድ እና መመዝገብ።
- ተገቢ የቁጥጥር እርምጀችን መምረጥ እና መተግበር።
- ያልተፈቀደለት ግቤት ለመከላከል የግቤት ፍቃድ ስርዓት ማቋቋም።
- ውስን ቦታ ውስጥ ለውስን ቦታዎች የሰለጠኑ ሰራተኖች ብቻ መግባታቸውን ማረጋገጥ።
- የአደጋ ጊዜ እቅድ እና አሰራር መበልፀጉን ፣ መግባባቱን እና መፈተኑን ፣ የአደጋ ጊዜ የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መከናወኑን እና የተሳተፉ ሰራተኞችን መቀላቀልላቸውን፣ የአደጋ ጊዜ ቁሳቁሶች መገኘታቸውን ማረጋገጥ ።

## 3.1 ተቆጣጣሪ/ለስራ ሃላፊነት የሚወስደው ሰው (PICW)

ተቆጣጣሪ/ለስራ ሃላፊነት የሚወስደው ሰው ለሚከተሉት ሃላፊነት ይወስዳል፡

- ከተወሰኑ ቦታዎች ግቤት ጋር የተያያዙ ተጋላጭነቶችን እና አደጋዎችን መለየት እና ያሉትን ወይም የታወቁትን ተጋላጭነቶች ለማስወገድ የትኞቹ የአስተዳደሪያዊ ወይም የምህንድስና መቆጣጠሪያዎች በጥቅም ላይ እንደሚውሉ መለየት።
- የተወሰኑ ቦታዎች ውስጥ የሚገቡ ሰራተኖች ሁሉ በስርዓት የሰለጠኑ እና ከተወሰኑ ቦታዎች ግቤት ጋር በተያያዘ ስላሉ አደነች ማወቃቸውን ማረጋገጥ።
- ፍቃዱን መቀበል እና ግቤትን መፍቀድ ከመጀምር በፊት ተገቢ የሆኑ ግቤቶች እንዳለ በፍቃድ መሆናቸውን፣ በፍቃዱ የተወሰኑት ፈተናዎች በሙሉ መካሄዳቸውን እና በፍቃዱ የተወሰኑ ሁሉም ሂደቶች እና መሳሪያዎች በቦታቸው ላይ መሆናቸውን ማረጋገጥ።
- እንደ አስፈላጊነቱ ግቤቱን ማቆም እና ፍቃዱን መሰረዝ ወይም ማገድ።
- የቡድን አባላትን ቁጥር ማረጋገጥ እና መቼም ብቻን መስራትን አለመፍቀድ።

## 3.2 ተቀጣሪ/ ሥራ ተቋራጭ

ተቀጣሪ/ ሥራ ተቋራጭ ለሚከተሉት ሃላፊነት ይወስዳሉ፡

- ከተወሰኑ ቦታዎች ግቤት ጋር በተያያዘ ሁሉንም አስፈላጊ የስልጠና ኮርሶች መውሰድ።
- ሁሉንም የደህንነት መሳሪያዎች እና የመከላከያ ልብሶች ለታሰበላቸው አላማ መጠቀም።
- ወደ ውስን ቦታ ከመግባት በፊት የመግቢያ ፍቃድ ማግኘትን ማረጋገጥ።
- በአስተዳዳሪዎቻቸው እናበፍቃድ ሰጪው እንደተሰመረው መመርያዎችን መከተል።
- ስራ ሲሰሩ ምንም አይነት አሳሳቢ ነገሮችን ወይም ችግሮችን ሪፖርት ማድረግ።

### 3.3 ቆሞ ተመልካች ሰው

ቆሞ ተመልካች ሰው ለሚከተሉት ሃላፊነት ይወስዳል፡

- ፍቃድ እና የስልጠና መዝገብ ጋር በተያያዘ የግቤት ፍቃድ በመፈተሽ የመግቢያ ቦታውን ከገቢው መቆጣጠር።
- የውስን ቦታውን የተሳታፊ መዝገብ መጠበቅ።
- እንደ ኦክሲጅን ደረጃ እና የመቀጣጠያ ክልል የመሳሰሉትን ከባቢያዊ አየር በመደበኛነት መከታተል እና መመዝገብ።
- በአከባቢያዊ መስፈርቶች መሰረት እንደ ደህንነቱን የጠበቀ የስራ አሰራር መሰረት የተወሰነውን ቦታ አየር ማናፈስ።
- በተወሰነው ቦታ የሚሰሩ ገቢዎች ጋር መነጋገር።
- በአደጋ ጊዜ ምላሽ በንቃት መሳተፍ።

## 4 አሰራር

### 4.1 የተወሰነ ቦታ ከማግባት በፊት

- ለተወሰነው ውስን ቦታ መግቢያ የተጋላጭነት ግምገማ ማካሄድ እና የመቆጣጠሪያ እርምጀች ማቋቋም/ማረጋገጥ። (ክፍል 6 ይመልከቱ)።
- ለተወሰነው ቦታ በቂ ብቃት (ክፍል 10 ይመልከቱ) እና የጤና ቁመና (ክፍል 5 ይመልከቱ) የትረጋገጠለት/ላት ብቁ የሆኑ ሰዎችን ለእያንዳንዱ ሚና እንደ PICW (ተቆጣጣሪ)፣ ተቀጣሪ(ዎች) እና ቆሞ ተመልካች ሰው መመደብ።
- ለስራው ተገቢ የሆኑትን መሳሪያዎች እና መገልገያዎች መምረጥ እና ጥሩ ትዕዛዝ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እነሱን መፈተሽ። (ክፍል 9 ይመልከቱ)
- ጥቅም ላይ መዋል የሚችለውን PPE መምረጥ እና ወደ ውስን ቦታ የሚገቡት ሰዎች እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው መሰልጠናቸውን ማረጋገጥ። (ክፍል 8 ይመልከቱ)
- እንደ ስራ ቦታው ባህር ፍላጎት እና አከባብቢያዊ ህጋዊ መስፈርቶች ከግቤት በፊት በተለያዩ ተገቢነት ባላቸው የከባቢ አየር ፈተኖች (ለምሳሌ  የኦክስጂን እጥረት ፣ መርዛማ ንጥረ ነገሮች እና ፈንጂዎች ስብስብ ወዘተ) የደህንነት ደረጃ ማረጋገጥ።
- የተወሰነ ቦታ ለመግባት ለሚያስቡ ሰዎች በሙል የመግቢያ ፍቃድ ማቅረብ። (ክፍል 7 ይመልከቱ)

### 4.2 በተወሰነ ስፍራ መግቢያ ስራ ወቅት

- ቆሞ ተመልካች ሰው በተወሰነው ቦታ ውጪ ወይም አቅራቢያ ሆኖ ሚናውን/ሚናዋን መጫወቱን/ቷን ማረጋገጥ። (ክፍል 3.3 ይመልከቱ)
- እንደ ስራ ቦታው ባህር ፍላጎት እና አከባብቢያዊ ህጋዊ መስፈርቶች መሰረት ከባቢ አየሩን እንደ የኦክሲጅን ደረጃ እና የተቀጣጣይነት ክልል በመደበኛነት መከታተል እና መመዝገብ።

## 5 የጤና አቋም እና ምላሽ

በተወሰነ ቦታ ውስጥ አቋማቸውን ማረጋገጥ እና ማፅደቅ የሚችሉ(ወይም እንደ አከባቢያዊ መስፈርቶች መሰረት የህክምና ፍተሻውን ያለፉ) ሰራተኞች ብቻ ወደ ተወሰነው ቦታ መግባት ይችላሉ። እንደ ተወሰነው ቦታ ሁኔታ ተጨማሪ ፍተሻዎች ሊጠየቁ ይችላሉ።

## 6 ተጋላጭነት ግምገማ እና እቅድ

የፕሮጀችት ተጋላጭነት ግምገማ ከስራ በፊት መሰራት አለበት እና በOHS የደህንነት እቅድ ውስጥ መካተት አለበት።

እንደተወሰነ ቦታ ወደተለየ ስፍራ ከመግባት በፊት ሊሰራ ያለው ስራ በብቂ ሁኔታ ሊለይ ይገባል። ስራው ከተለየ በኋላ አስተዳዳሪዎች መቼ ስራው ከተወሰነው ቦታ ውጪ መሰራት እንደሚቻል በግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። ስራው ወደተወሰነው ቦታ ውስጥ ሳይገቡ በስኬት መጨረስ መቻሉን ከተረጋገጠ የሚከተለው አሰራር አያስፈልግም።

የተወሰነ ቦታ የተጋላጭነት ግምገማ/ፍተሻ በተወሰነው ቦታ ውስጥ ስራ ሳይጀመር በፊት መደረግ አለበት። የተጋላጭነት ግምገማው በሚሰራው ስራ ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ማንኛቸውንም የድንገተኛ አደጋ ሁኔታዎች ሊያካትት ይገባል። የድንገተኛ አደጋ አቀማመጦች ለሚሰራው ስራ እና ለመግቢያው ጊዜ እና ቀን የተለዩ መን አለባቸው።

የተወሰነ ቦታ ስራ ሲካሄድ በሁሉም ጊዜ ቆሞ ተመልካች ሰው መገኘት እንዳለበት ልብ ሊባል ይገባል።

## 7 የመግቢያ ፍቃድ

የተወሰነ ቦታ ለመግባት ለሚያስቡ ሰዎች የመግቢያ ፍቃድ እንዲሰጥ ያስፈልጋል። የተወሰነ ቦታ ፍቃድ ለአንድ ፈረቃ ብቻ ሊሰጥ ይገባል እና የተወሰኑ ቦታዎች ሁኔታዎች አብዛኛውን ጊዜ ቋሚ ስላልሆኑ በየፈረቃው ሊከለስ ይገባል።

የተወሰኑ ቦታዎች መግቢያ ፍቃዶች ለደህንነቱን ለጠበቀ ግቤት እና የስራ አፈፃፀም ቅድመ ጥንቃቄዎች እና ግልፅ መመርያዎች ሊያካትቱ ይገባል። በፍቃድ መስጫ ጊዜ ወቅታዊ ፍተሻዎች ወሳኝ ናቸው።

በተወሰነው ቦታ ውስጥ ለስራው የቀጥታ ቁጥጥር ሃላፊነት የሚወስደው ሰው (በተለምዶ በቦታው ላይ ያለ ተቆጣጣሪው ወይም PICW) የመግቢያ ፍቃድ ሊሰተው ይገባል። የተወሰነው

በታ ውስጥ ማን እንደሚገባ ሊመዘግቡ ይገባል። የመግቢያ ፍቃዶች በስራ በታው ላይ ሊፃፉ እና ሊለጠፉ ኣና ለሁሉም የቡድን አባላት ሊነገር ይገባል።

ወደ ተወሰነው በታ የሚገቡ ሰዎች ስለ መግቢያ ፍቃዱ ይዘቶች ሊያውቁ፣ ሊረዱ እና ሊስማሙ ይገባል።

## 7.1 የመግቢያ ፍቃድ አስገዳጅ ይዘቶች

- የሚገባበት የፍቃድ ስፍራ፣ የተፈቀደለት/ላቸው ገቢ/ዎች፣ የገቢ ተቆጣጣሪዎች ለመሆን ፍቃድ ያላቸው ብቁ ተሳታፊዎች እና ግለሰቦች ስም።
- የከባቢ አየር ፈተና መመዘኛ እና ውጤት።
- የፈታኝ ስም ወይም ፊርማ።
- ግቤትን የሚፈቅደውን ሰው ስም እና ፊርማ።
- የግቤት ምክንያት እና የታወቁ የስፍራው አደጎች።
- የፍቃድ ስፍራዎችን ለመለየት እና የስፍራውን አደጎች ለማጥፋት ወይም ለመቆጣጠር የሚወሰዱ እርምጃች።
- የነፍስ አድን እና የአደጋ ጊዜ አገልግሎቶች ስም እና የስልክ ቁጥሮች እና እነሱን ለማግኘት መጠቀም የሚቻልባቸው መንገዶች።
- ቀን እና የተፈቀደለት የግቤት የሰዓት ገደብ።
- ተቀባይነት ያላቸው የግቤት ሁኔታዎች።
- የግንኙነት አሰራሮች እና በግቤት ጊዜ ግንኙነት ለመጠበቅ የሚያስፈልግ መሳሪያ።
- ተጨማሪ ፍቃድ እንደ ለሙቀት ስራ በፍቃዱ በታ ውስጥ ስራ ለመስራት ፈቃድ የሰጠ።
- የግል መከላከያ መሳሪያዎችን እና የማንቂያ ስርዓቶችን ቸምሮ ልዩ መሳሪያዎች እና አሰራሮች።
- የተቀጣሪን ደህንነት ለማረጋገጥ ሌላ ምንም አይነት መረጃ።

# 8 የግል መከላከያ መሳርያ

በተወሰነው ስፍራ ስራ እንዲሰሩ የሚያስፈልጉት ሰራተኞች ተገቢውን አስፈላጊ PPE መልበስ እና PPE እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው መሰልጠን አለባቸው።

## 8.1 የPPE ልየታ እና ምርጫ

- ለተወሰነ ስፍራ ግቤት ተገቢነት ያለውን PPE ልየታ ከቁስ፣ ከባቢ አየር፣ በስፍራው በተለምዶ ያሉ ሁኔታዎች እና በታቀደው ስራ መሰረት ይሆናል።
- አንዴ የPPE እና የእስትንፋስ ጥበቃ ደረጆች ከተወሰኑ በኋላ አደጎች እንደገና ተገምግመው እና በሰጪው / በተጋላጭነት ገምጋሚ ቡድን ዝቅ ላለ የጥበቃ ደረጃ ተገኝቶ ካልተወሰነ ሊላሉ አይገባም።
- በግዳጅ አየር ማናፈሻን በመጠቀም የተሻሻለው ከባቢ አየር አደጋዎቹ እንደገና ከመገምገማቸው በፊት ወደ የተረጋጋ ደረጃ መድረስ አለበት።
- በመካሄድ ላይ ያለው የግዳጅ አየር ማናፈሻ፣ በቦታው መኖር ካለበት የአየር ማናፈሻ ክፍሉ እንደሌለ ሆኖ ግምገማው መከናወን አለበት።
- በኦክሲጅን እጥረት ባለባቸው ከባቢ አየሮች፣ መርዛማ ነገሮች ከደፍ ግድብ ትመና (TLV) በላይ ሲሆኑ እና በመጀመሪያ በውስን ቦታ ውስጥ ያለው ከባቢ አየር ደህንነቱ ተረጋግጦ ነገር ግን ግቤት በትፈቀደበት ወቅት ደህንነቱ እንዳልተረጋገጠ ለማመን ምክንያቶች ሲኖሩ (ለምሳሌ ከጭቃው ወይም በቦታው ውስጥ ወይም በብየዳ ጭስ ውስጥ ከሚገኙትን ተቀማጭ ዝቃጮች ከሚወጣው ጭስ) ገቢዎች አየር የሚሰጡ ማስተንፈሻዎችን ይለብሳሉ።
- በምንም አይነት ሁኔታ የኬሚካል ቀላህ/ታሳ አይነት የጋዝ ጭንብል ለተወሰነ በታ ግቤት ጥቅም ላይ እንዳይውል። ካስፈለገ የጥቃቅን ቅንጣቶች ማስተንፈሻ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።
- ተቆጣጣሪው/PICW አየር አቅራቢ አስተንፋሾች (የአየር ጭንብሎች ወይም በራስ የተያዘ የመተንፈሻ መሳሪያ) በጥሩ ሁኔታ ላይ እንዳሉ፣ በስርዓት መያዛቸውን እና እንደአምራቹ ውሳኔዎች መገምገማቸውን ያረጋግጣል።
- ተቆጣጣሪው/PICW የመተንፈሻ መሳሪያ ተጠቃሚዎች መተንፈሻ መሳሪያውን ለመጠቀም በህክምና የተረጋገጡ እና የሰለጠኑ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ።
- ወዲያውኑ ለሕይወት እና ለጤንነት አደገኛ (IDLH) በሆነ ከባቢ አየር ገቢዎች በራስ-የተያዘ የመተንፈሻ መሳሪያ (SCBA) ወይም ከቋሚ የማምለጫ ስብስብ ጋር የተያያዘ የአየር መንገድ ጭምብል ይለብሳሉ። የነፍስ አድን ድልደላዎች በቀላሉ ሊገኙ ይገባል።
- የነፍስ አድን ቀረጢት እና የእሳት ማጥፊያ በቀላሉ ሊገኙ ይገባል።

# 9 መሳሪያዎች እና መገልገያዎች

በተወሰነው ቦታ ውስጥ ጥቅም ላይ ለመዋል ሁሉም መሳሪያዎች እና መገልገያዎች (የመብራት ስርዓቱንም ጨምሮ) ለስራው ከባቢ አየር እና ለስራው የተመቻቹ መሆናቸውን ለማረጋገጥ በአከባቢያዊ የህግ አስፈላጊ ነገሮች እና መስፈርቶች መሰረት ሊመረጡ ይገባል።

መሣሪያዎቹ እና መገልገያዎቹ ከእያንዳንዱ አጠቃቀም በፊት ምርመራ ይደረግባቸዋል እንዲሁም በጥሩ ሁኔታ ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የአምራች ምክሮችን ተከትሎ በመደበኛነት ይጠበቃሉ።

## 10 ስልጠና

ለተወሰኑ ቦታ መግቢያ ተቆጣጣሪዎች፣ ለተፈቀደላቸው የተወሰኑ የቦታ ገቢዎች፣ ከባቢ አየሩን የሚፈትን ወይም የሚከታተል ሰው፣ ቆሞ ተመልካች ሰው/ ተሳታፊ እና ለአደጋ ሠራተኞች በቂ የቴክኒክ ብቃት መረጋገጥ አለበት።

በተወሰኑ ቦታዎች የሰለጠኑ ሰዎች ብቻ ስራ ሊያካሂዱ ይገባል። የስልጠና መዝገብ ሊጠበቅ ይገባል፣ የምስክር ወረቀቶች እና ቀጠሮዎች ተቀባይነት ያላጸው እና የዘመኑ መሆነ አለባቸው።

የተወሰነ ቦታ እንደገቡ ተቀጣሪዎች በሚከተሉት በብቃት መሰልተን አለባቸው፡

- የውስን ስፍራዎች አደጎች፣
- የአሰራር ግምገማ፣
- የቁጥጥር እርምጆች፣
- የአደጋ ጊዜ እቅድ እና አሰራሮች፡ እና
- የደህንነት መሳሪኢያዎች ምርጫ፣ ጥቅም እና ተስማሚነት።

የነፍስ አድን ስልጠና ወሳኝ ነው እና ቡድኑ ተገቢውን የነፍስ አድን ስልጠና ሊኖረው ይገባል።

## 11 ክትትል እና ግምገማ

የOHS የደህንነት እቅድ በፕሮጀክቱ ፍፃሜ እና በኋላ ሊዘምን እና ሊገመገም ይገባል እና ሃልፊነቱ ላለበት/ባቸው ተቆጣጣሪ(ዎች) ሊብኣ ይገባል።

የመግቢያ ፍቃድ በመደበኝነት ሊገመገም ይገባል። ፍቃድ በከፍተኛው አንድ (1) ፈረቃ ሊሆን ይገባል እና ለእያንዳንዱ ፈረቃ ሊገመምገም ይገባል።

## 12 መዝገቦች

ሁሉም መዝገቦች ከOHS የድህንነት እቅድ መስፈርቶች ጋር በተዛመደ መልኩ ሊቀመጡ ይገባል።

የመግቢያ ፍቃዶች በቦታው ላይ ሊለጠፉ እና በስራው ወቅት ሊታዩ ይገባል። ሁሉም ፍቃዶች የሚያዙ ይሆናል።

## 13 የለውጥ መረጃ

ይህ የዚህ መስፈርት የመጀመሪያው ስሪት ነው።